አዋጅ ቁጥር -------/2010

**<u>የኢነርጂ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ</u>**

የኢነርጂ አዋጅን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **<u>...አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የኢነርጂ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ---------/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ማሻሻያ</u>**

የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

1/ የአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (9) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀጽ (9) ተተክቷል፤

"9/ 'የኤሌክትሪክ ሥራ' ማለት የኤሌክትሪክ ዲዛይን፣ ኢንስታሌሽን፣ ጥገና፣ ፍተሻ፣ መቆጣጠር፣ ተቋራጭነት፣ ወይም ማማከር፣ የኤሌክትሮ መካኒካል ሥራ ወይም ማንኛውም ሌላ የኤሌክትሪክ ነክ ሥራ ነው፤"

2/ ከአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (4) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (5)፣ (6) እና (7) ተጨምረዋል፤

"5/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (3) ወይም (4) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ባለፈቃድ ሥራ ያልጀመረው ከአቅም በላይ በሆነ አስገዳጅ ምክንያት መሆኑን ማመልከቻ አቅርቦ ባለስልጣኑም ይህንኑ ካረጋገጠ ፈቃዱን ለሁለት ጊዜ ብቻ በየዓመቱ ሊያድስ ይችላል፡፡

6/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃድ ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ ሥራውን ሳይጀምር ከቀረ ወይም በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ (3) ወይም (4) የተደነገገውን ሁኔታ ያላከበረ እንደሆነ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

7/ ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ (3) ወይም (4) መሠረት በፈቃዱ ላይ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራ መጀመሩን ለባለስልጣኑ በሪፖርት ካሳወቀ፣ እንደሁኔታው ባለሥልጣኑ ክትትል አድርጎ ማረጋገጡ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፈቃድ ዘመኑ ባለፈቃዱ ሥራ ስለመጀመሩ ሪፖርት ካደረገበት ጊዜ ጀምሮ የሚቆጠር ይሆናል፡፡"

www.chilot.me

3/ የአዋጁ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (3) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) ተተክቶ፣ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4) ተጨምሯል፤

“3/ ከጂኦተርማል ወይም ከውሃ ኃይል ኤሌክትሪክ በማመንጨት፣ ለማስተላለፍ፣ ለማከፋፈል እና ለመሸጥ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ ፈቃድ የወሰደ ማንኛውም ሰው ፈቃዱን ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራ መጀመርና ሥራውን ስለመጀመሩም ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

4/ ከፀሐይ ኃይል፣ ከንፋስ፣ ከባዮማስ፣ ከድንጋይ ከሰል፣ ከተፈጥሮ ጋዝ ወ.ዘ.ተ. ኤሌክትሪክ ለማመንጨት፣ ለማስተላለፍ፣ ለማከፋፈልና ለመሸጥ፣ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር ለመላክ ፈቃድ የወሰደ ማንኛውም ሰው ፈቃዱን ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራውን መጀመርና ሥራውን ስለመጀመሩም ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡”

## 3. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ----------ቀን 2010 ዓ.ም.

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት

www.chilot.me